

# የፍጥረት ታሪክ

* ምድርና በእርስዋ ውስጥ ያሉ ነገሮች ከመፈጠራቸው በፊት እግዚአብሔር ነበር።

* **በመጀመሪያው ቀን** እግዚአብሔር “ብርሃን ይሁን አለ።” ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው። ጨለማውን ደግሞ ሌሊት ብሎ ጠራው።

* **በሁለተኛው ቀን** እግዚአብሔር ሰማይን ሰራ።

* **በሶስተኛው ቀን** እግዚአብሔር የብስን (ምድርን) ከውኆች ለየ። እንዲሁም አበቦችን፣ ዛፎችንና ሳርን ፈጠረ።

*. **በአራተኛው ቀን** እግዚአብሔር ፀሐይን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን ፈጠረ።

* **በአምስተኛው ቀን** የሰማይ አእዋፍና በውኃ ውስጥ የሚዋኙ አሳዎችን ፈጠረ።

* **በስድስተኛው ቀን** እግዚአብሔር እንስሳትን ፈጠረ። እንዲሁም እርሱን የሚመስሉ ሰዎችን ፈጠረ። እግዚአብሔር ወንዱን አዳም ብሎ ሲጠራው አዳም ደግሞ ሚስቱን ሔዋን ብሎ ጠራት።

*  በሰባተኛው ቀን እግዚአብሔር አረፈ። የፈጠረውን ነገር ሁሉ ተመልክቶም ሁሉ መልካም እንደሆ አየ።

* ለሰራቸው ወንድና ሴት ሰዎች እግዚአብሔር መኖሪያ ይሆናቸው ዘንድ ኤደን ገነትን እግዚአብሔርም በገነት ከሚገኙት ዛፎች ሁሉ ፍሬ መብላት እንደሚችሉ ነገራቸው። ሆኖም ክፉንና መልካምን ከሚያስለየው ዛፍ ፍሬ እንዳይበሉ። አዘዛቸው።  ሆኖም እባብ የሚባለው ፍጥረት ሔዋንን አታለላትና እንዳይበሉ ከታዘዙት የዛፍ ፍሬ በላች።  ለአዳምም ከዚህ የዛፍ ፍሬ ሰጠችውና በላ። እግዚአብሔርን ስላልታዘዙት ከሚያምረው ቤታቸው ተባረሩ።  ከዚህ በኋላም ከባድ ስራ መስራት ጀመሩ። ብዙ ችግርም ገጠማቸው።

* እግዚአብሔር የሚለውን መስማት ሁሌም ጠቃሚ ነው።

የፍጥረት ታሪክ የሚገኘው በመፅሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት መፅሐፍ በምዕራፍ 1፣ 2 እና 3 ነው።

http://gardenofpraise.com